የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር ዐFAGF 06.8/2/21
ቀን 10/08/2014

ለሀረማያ ዩኒቨርሲቲ

ሀረማያ

ጉዳዩ፡- የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 11 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፤ 36 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 20 ገጽ አባሪ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡ በመሆኑም በገጽ 68 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር መርሃ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
# የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው 1146/2011) ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- ☞ በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- ☞ የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- ☞ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል:: የሂሳብ ሪፖርቱ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆን በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው:: የሚከተሉት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- ☞ የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ☞ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- ☞ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ☞ የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ☞ የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ☞ የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የመመረቂያ ፅሁፍ ለመፈተን የመጡ መምህራን በመመሪያ ከተፈቀድ የአልጋ፣ የትራንስፖርት እና የምግብ መስተንግዶ ውጭ ለ133 ከተለያዩ ኮሌጅና ዲፓርትመንቶች ለመጡ እንግዶች በሚል በአዲስ አበባ የአበል ተመን መሰረት አድርጎ ለእያዳንዳቸው የ4ቀን አበል በማሰብ በድምር ብር 396,028.00 ከተቀመጠው ደንብና መመሪያ ውጭ ክፍሎ በመገኘቱ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ አድርጎታል::

2. ዩኒቨርሲቲዉ የመመረቂያ ፅሁፍ ለፈተኑ መምህራን የስራ ግብርን ጨምሮ በድምሩ ብር 2,986,275.00 ክፍሎ መዝገቦ ሪፖርት ማድረግ ሲገባ ታክስ ወጪቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል በድምሩ ብር 4,373,580.11 ክፍሎ መዝገቦ ሪፖርት በማድረጉ በብልጫ ብር 1,387,004.84 የተከፈለ

መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 2,986,275.00 ላይ የስራ ግብር ብር 1,036,196.25 ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ፣ ሁኔታዉ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ ያደረገና መሰብሰብ የነበረበት የስራ ግብር ገቢ እንዳይሰበሰብ አድርጎታል፡፡

3. በዋና ግቢ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱን ለመከታተል የመጡ የወጪ ሀገር ዜጋ በሐረር ከተማ ውስጥ የሚገኘውን የአቶ ብሩ ነጋያሲማ መኖሪያ ቤት ተከራይተው ለግለሰቡ በወር 30,000.00 በማስብ የዘጠኝ ወር ብር 270,000.00 ከደንብና መመሪያ ወጪ ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ በመገኘቱ የመደበኛ ወጪ ያለአግባብ በዚህ ገንዘብ መጠን ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርጎታል፡፡
4. በማፅቀፍ ግዥ መፈፀም ሲገባ አላግባብ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዢ በመፈፀሙ ምክንያት በድምሩ ብር 509,342.67 ያለአግባብ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡
5. ቀጣይነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች ቋሚ የሥራ መደብ ጥናት በማድረግ መዋቅር በሚኒስቴሩ በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በዋና ግቢ ብር 5,219,127.32፣ ከዚህ ውስጥ ብር 1,007,202.56 ለተማሪዎች ካፍቴሪያ ሰራተኞች በሪፈራል ሆስፒታል ብር 743,900.00 በድምሩ ብር 5,963,027.32 በቀን ሠራተኝነት ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ሰራተኞቹ በሰዓቱ ገብተዉ ለመስራታቸዉ የሚቆጣጠሩበት የሰዓት መቆጣጠሪያ የፊርማ ሰነድ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ኃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሠራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ መሆኑ፣

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም::

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1.ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

1.1 ዘላቂነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች ላይ ለአንድ ዓመት የኮንትራት ሰራተኞችን በመቅጠር በዋና ግቢ ብር 152,811.00፣ በሪፈራል ሆስፒታል ብር 1,374,183.00 በድምሩ ብር 1,526,994.00 ክፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

1.2 በድምሩ ብር 953,289.50 የዉሎ አበል የጉዞ አላማ ሳይገለጽ እና የዉሎ አበል ቅጽ ሳይኖር የተከፈለ መሆኑ፣

1.3 በዋና ግቢ በግቢው ውስጥ ላሉ ተሽከርካሪዎች በተለያየ ጊዜ ወደ ካምፓኒዎች ውስጾ ሲያስጠግን ተቀየረ ለተባለው የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ብር 865,236.20 ክፍያ ሲከናውን ተጠገነ ለተባለው ተሽከርካሪ የአሮጌ ተመላሽ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልቀረበ በመሆኑ፣

1.4 በድምሩ ብር 1,637,990.70 ዝርዝር የጥገና ሥራ ማስረጃ ሳይኖረው የጥገና ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

1.5 በድምሩ ብር 2,614,736.00 በትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደብ አለመመዝገቡ፣

1.6 ዩኒቨርሰቲው የሞተር ብስክሌቶች ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፍቃድ ሳያገኝ በተለያዩ ግዜ በዋጋ ማውዳደሪያ የግዥ ዘዴ በመጠቀም በብር 679,025.00 ሞተር ብስክሌቶችን ግዥ ፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፣

1.7 ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል ዳቦ የብር 716,525.00 ግዥ ያለጨረታ (ያለዉድድር) በቀጥታ ከአንድ ድርጅት ግዥዉ የተፈፀመ በመሆኑ መንግስት ከጨረታ ግዥ ማግኘት የሚገባዉን ጥቅም አሳጥቶታል፡፡

1.8 በድምሩ በብር 510,583.50 የተገዙ ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተገቢው ስፔስፍኬሽን ሳይወጣለት ግዥ ተፈጽሞ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

1.9 በዋና ግቢ ብር 437,950.00፣ በጤናና ህክምና ሰይንስ ኮሌጅ ብር 170,775.00 በድምሩ ብር 608,725.00 በተለያዩ ጊዜ የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ሲያወጣ የአምራቾችን የንግድ ምልክት (ብራንድ) በመጥቀስ ግዥዉ የተፈጸመ መሆኑ፣

1.10. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተዉ ሂሳብ ዉስጥ ከ1 ዓመት እስከ 10 ዓመት በተሰብሳቢነት የቆየና በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 56,460,864.17 መኖሩን ተረጋግጧል፡፡

1.11. በድምሩ ብር 15,603,602.64 ለባለመብቱ በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሒሳብ  መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.12. በጠቅላላ ድምር ብር 355,980,834.70 ለየሂሳብ ኮዶቹ የተደለደለዉ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

2.1 <u>ንብረት</u>፣

<u>በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ፣</u>

<u>በዋና ግቢ፤</u>

**በዋና ግቢ ቋሚ ንብረት እስቶር በተመለከተ፤**

- ☞ በቋሚ ንብረት እስቶር ዕቃዎች በአይነት እና በመጠን ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ፣
- ☞ ቋሚ ንብረት እሰቶር ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ በእቃዎች ላይ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- ☞ ቋሚ ንብረት እሰቶር ክፍል ውስጥ በኤሲቲ ፕሮጀክት ማለትም ዳታ ሴንተር፣ሰርቬላንስ ኮሜር እና ዋን ካርድ ሲስተም የፕሮጀክት እቃዎች ክምችት መኖሩ እና በስርዓት ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ☞ በቋሚ በንብረት የካይዘን አሰራር ሰርዓት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ አለመደረገ በተመለከተ፣
- ☞ በዩኒቨርሰቲው የአሮጌ ዕቃ ተመላሽ  ሳልቫጅ እስቶር የሌለው መሆኑ፣

**በዋና ግቢ የአልባሳት እስቶር በተመለከተ**

- ☞ በአልባሳት እሰቶር ውስጥ የንብረት መደርደሪያ ሽልፎች የሌሉት መሆኑ፣
- ☞ በዩኒቨርስቲው በአልባሳት እስቶር ውስት እቃዎች በአይነት በአይነት ፣በመጠን ያልተቀመጡ መሆኑ፣

☞ በዩኒቨርስቲው በአልባሳት እስቶር ውስጥ ቢን ካርድ እቃዎች ላይ የማቀመጥ መሆኑ፣

**በዋናግቢ የአላቂ ንብረት ክፍል እስቶር በተመለከተ**

☞ በአላቂ ንብረት እስቶር ውስት የእቃ መደርደሪ ሙሉ በሙሉ ያልተሟላ እና በአይነት እና በመጠን ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፣

☞ በአላቂ ንብረት እስቶር ስቶር ውስጥ ብዛት ያለው በግምት ሀምሳ (50) የሚጠጋ ሳኒታይዘር ወጭ ሆኖ በእስቶር የሚገኝ መሆኑ፣

☞ በአላቂ ንብረት እስቶር ውስጥ ቢንካርድ ላይ የተመዘገበው ክላሰር 12 እሽግ ውይም ጥቅል ቢያሳይም በቁትር የተገኘው ግን 15 መሆኑ እና ትርፍ 3 ቱ እሽግ በትክክል ያልተመዘገበ መሆኑ፣

☞ በአላቂ ንብረት እስቶር ውስጥ 15 ቦክስ ፋይል ወጭ የተደረገ ቢሆንም በእስቶር ውስጥ የተገኘ መሆኑ፣

☞ በአላቂ ንብረት እስቶር እስቶር ውስጥ በቁጥር 156 የእርሳስ መቅረጫ ከሶስት አመት በላይ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑበአላቂ ንብረት እስቶር ውሰጥ በቁጥር 172 ፍሬ ስካች ከተር ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በእስቶር ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>በጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ሪፈራል ሆስፒታል</u> **አላቂ እናቋሚ እስቶር በተመለከተ**

☞ በዩኒቨርሰቲው ሪፈራል ሆስፒታል የአላቂና ቋሚ ንብረት እስቶር ክፍል በአንድ ክፍል ውስጥ የሚቀመጡ መሆኑ፣

☞ ንብረት ከዋና ግቢ በሞዴል 22 ወጪ ተደርጎ በሪፈራል ሆስፒታል ሞዴል 19 የሚቆረጥለት መሆኑ አንድ እቃ በአንድ ተቋም ሁለቴ ምዝገባ የሚደረግ መሆኑ፣

☞ በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል በእርዳታ ገቡ እቃዎችየዋጋ ተመን ሊዎጣላቸው ሲገባ ያልወጣላቸው ስለመሆኑ ለአብነት በሞዴል 19 ቁጥር 371251 በቀን 03/01/13 ገቢ የሆኑ ብሊች 0.5 ብዛት8 እና ሳሙና ብዛት 400 ወዘተ፡፡

- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል የእስቶር ጥበት ስላለ ቋሚ ንብረት ፤አላቂ እና የፅህፈት መሳሪያዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው መገኘቱ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል አውቶ ክሌቭ ማሽን ብዛት ሁለት በብልሽት ምክንያት ተጠግነው አግልግሎት መስጠት እየቻሉ በቋሚና አላቂ እስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል ቢን ካርድ በእቃዎች ላይ የማይቀመጥ ስለመሆኑ እና በተሟላ መልኩ የቢን ካርድ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል የንብረት አያያዝና አጠቃቀም በተሟላ መልኩ በካይዘን መልክ አደረጃጀት አለመሆኑ፣
- የፅዳት እቃዎች ክምችት ከፍተኛ በመሆኑ እስቶሩን እያጣበበ እንደሚገኝ መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል ሰራተኛች ለተሞክሮ ወደ ሌላ ቦታ ሂደው ልምድ ልውውጥ ያላደረጉ እና የንብረት አያያዝ ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል የአሮጌ እቃ ተመላሽ እስቶር በአግባቡ የሌለ ስለመሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ሪፈራል ሆስፒታል በቋሚ እና አላቂ እስቶር የተሟላ የሰው ሀይል አለመኖሩ፣

**በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በቋሚ እና አላቂ እስቶር በተመለከተ**

- በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአላቂ እስቶር ውስጥ የተሟላ የሰው ሂል አለመኖሩ፣
- በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሊወገዱ የሚገባ ሁለት ኮምፒውተር እና ሁለት ሪሲቨር ያልተወገዱ መሆኑ፣

**በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአልባሳት እስቶር በተመለከተ**

- በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአልባሳት እስቶር ውስት መደርደሪያ የሌለ መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአልባሳት እስቶር ውስጥ እቃዎች በአይነት በአይነት በመጠን ያልተቀመጡ መሆኑ፣

☞ በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአልባሳት እስቶር ውስጥ ቢን ካርድ እቃዎች ላይ የማይቀመጥ መሆኑ፣

☞ በዩኒቨርስቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአልባሳት እስቶር ውስጥ ወቅታዊ የቢን ካርድ የማቀናነስችግሮች ያሉመሆኑ በኦዲት ወቅት ተርጋግጧል

**ተሽከርካሪን በተመለከተ**

☞ በዩኒቨርርስቲው ስም ተመዝግበው የሚገኙ ብዛት 26 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ለረጅም ጊዜ በብልሽት አገልግሎት የማይሰጡ እና ሊዎገዱ የሚገባ ቢሆንም ሳይዎገዱ ለረጅም አመታት የቆዩ መሆኑ፣

☞ አምስት ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በብልሽት ምክንያት ከ አንድ ዓመት በላይ ሳይጠገኑ በግቢ ውስጥ የቆሙ መሆኑ፣

☞ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ውስጥ ንብረት ተመላሽ ማለትም የተሽከርካሪ መለዋዎጫ(ስፔር ፓርት) በጋራዥ እስቶር ውስጥ የሚገኝ እና ሞዴል 19 የማይቀረጥለት መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

☞ በአጠቃሊይ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ እና ከላይ በተገለጹት ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ሊከሰት የሚችል ችግሮችን በመለየት ተስማሚ የጸደቀ የአፈጻጸም የውስጥ መመሪያዎች የሌሉት መሆኑ፣

2.3 የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሰው ሀብት መረጃዎችን በተደራጅ እና ቴክኖሎጅን መሰረት ያደረግ ኤክትሮኒክስ ሲስተም ያልተደራጀ እና መረጃወች በዓላዊ አሰራሮች የሚከተል መሆኑ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው አብዴት የማይደረግ መሆኑ፣

**የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ፤**

**በ2012 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች**

☞ በድምሩ ብር 245,550.45 ከሆስፒታሉ ውስጥ ገቢ በጀት ለሕይወት ፋና ሆስፒታል ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር፣ ዳይሬክተሮች፣ ተወካይ ዳይሬክተሮች እና ኬዝ ቲም ኃላፊዎች አላግባብ በሚመለከታው አካል

ያልተፈቀደ ክፍያ እና የሆስፒታሉ ቦርድ መወሰን በማይችልበት ሁኔታ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

☞ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 376,433.25 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣

☞ ለመኖ አገልግሎት የተከፈለው ብር 2,083,502.60 ላይ መቀነስ የነበረበት ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 135,880.60 ተጨማሪ እሴት ታክስ በመመሪያ መሠረት በአግባቡ ያልተቀነሰ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

☞ ለብሩ ነገያ ሲማ የቤት አከራይ የቤት ክራይ አገልግሎት ግዥ ክፍያ ስፈጸም የቀረበዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተከታታይ ቁጥር የለሌዉ መሆኑና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለሌላቸዉ 30% withholding tax ተቀናሽ በማድረግ ክፍያ መፈጸም ስገባዉ አለአግባብ ብር 36,000.00 ሳይቀነስ ለድርጅቱ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

☞ የለስላሳ ባዶ ሳጥን ማስያዣ ሂሰብ በሳጥን ብር 300.00 የሳጥን ብዛት 420 በድምሩ ብር 126,000.00 ሳጥን ሲመለስ ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ክፍያ እንዲፈጸም በአስተዳደር ተማ/ጉዳይ ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ፍቃድ የተሰጠና ክፍያ ለሙሜ አዱስ ሱሌይማን ካፍቴሪያ የተፈፀመ ሲሆን ነገር ግን ሂሳቡ ሲወራረድ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲኖርበት የክፍያው ሃሳብ ተቀይሮ ወደ ኪራይ በመቀየር ለድርጅቱ ባቀረበው ደረሰኝ መሰረት ክፍያው አለአግባብ ወደ ወጪ የተቀየረ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

☞ በዋናው ግቢ ለምድረ ግቢ ውበትና ጽዳት እና ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት በቀን ሠራተኝነት ለሠሩ ብር 508,452.00 እና በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለሆስፒታል ለተለያዩ ሥራ በቀን ሠራተኝነት ለሠሩ ብር 165,000.00 በድምር ብር 673,452.00 ለተለያዩ ለቀን ሠራተኞች ክፍያው ሲፈፀም ሰራተኞቹ ስራቸውን በትክክል ስለመስራታቸው የሚያረጋግጥ የቀን ሠራተኞቹ ፊርማና የሀጋዊነት

ማስረጃ ማለትም መታወቂያ ከወጪ ሰነድ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑን የወጪው ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ☞ ብር 944,793.07 ለተለያዩ ተቋማት አገልግሎት ለተፈፀሙ ክፍያዎች ተገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
- ☞ በድምሩ 1,058,270.68 ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን ተሰብሳቢ ሂሳቡ ተመላሽ ሳይደረግ ውል የተቋረጠ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>**በ2011 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች**</u>

- ☞ ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ከተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 4,860,085.55 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ለክፍያ የእጅ በእጅ ሽያጭ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባ አላግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳቡ የተወራረደና በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ☞ ኤም ትራክሽን በዋናው ግቢ ውስጥ በሚገኘው የመምህራን መኖሪያ ቤት ጥገና በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0030 ብር 2,273,748.16 ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ የሚታይ መሆኑና በዩኒቨርሲቲው ለደረሰው ኪሳራ ውሉን ባቋረጠው ህንጻ ተቋራጭ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን በባለፈው በጀት አመት የተገለጸ ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

<u>**የ2010 በጀት አመት ኦዲት ግኝቶች**</u>

- ☞ በ2010 በጀት አመት በዩኒቨርሲቲው የሚመጡ እንግዳ መምህራን ከሚያገኙት ጥቅም ወይም ገቢ ላይ የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው ቅድመ ታክስ 2% (ሁለት በመቶ) በመቀነሱ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 1,083,866.02 ልዩነት በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ☞ በ2010 በጀት አመት ለመምህራን ሳይፈቀድ ኮሌጁ ለህክምና ት/ቤት መምህራን ኢለቨናይዜሽን የደመወዛቸውን 11% በየወሩ በመክፈል በድምሩ ብር 467,656.75 አለአግባብ ከመመሪያ ውጪ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

☞ በ2010 በጀት አመት በድምሩ ብር 822,787.36 ከተለያዩ ድርጅቶች የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

**በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!**

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክተር

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

[illegible] 2014

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
## የ 2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

**መግቢያ፤**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲዉን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

**ዓላማ፤**

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲዉ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፤
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የ 2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የወጪ ሂሳብ፣**

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፣ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውንና እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1. **የኮንትራት ቅጥርን በተመለከተ፣**

1.1.1. **ግኝት፣**

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተጻፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለዉና በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች ተቀጥረዉ ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሰራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለዉ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ተቀጥረዉ የነበሩ ሰራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸዉ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈጻጸም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት /ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄዉ በመጀመሪያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች ላይ ለአንድ ዓመት የኮንትራት ሰራተኞችን በመቅጠር በዋና ግቢ ብር 152,811.00፣ በሪፈራል ሆስፒታል ብር 1,374,183.00 በድምሩ ብር 1,526,994.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ የሂሳብ ዝርዝር ሁኔታዉ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- **በዋና ግቢ** በቴክኖሎጅ ተቋም በምግብ ቴክኖሎጂ ሂደት ምህንድስና ት/ክፍል ባለሙያዎች ለአንድ አመት የሚታድስ በግቢው የኮንትራት ሰራተኞችን በመቅጠር በቀን 28/11/2012 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ 241379 በሂሳብ መደብ 6113 ብር **152,811.00** በክፍያ እንደፈፀመ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- **በሪፈራል ሆስፒታል** በፋይናንስ፣ በግዥ፣ በጠቅላላ አገልግሎት፣ በተቋማ ለውጥ ክፍል፣ ሀብት ክፍል፣ በፋርማሲ፣በኒው ኤት፣በኤም ሲ.ኤች ክፍል ፣አንስቲዣ ክፍል፣በስረጅካል ክፍል፣አይ.ሲ.ዩ እና በኢመርጅንስ ክፍል የቋሚ የስራ መደቦች በኮንትራት ቅጥር ተሞልተው እና ለአንድ አመት የሚቆይ የኮንትራት ቅጥር ብር 1,374,183.00 ተከፍሎ ተገኝቷል ፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)**

1.1.2. <u>ሥጋት፣</u>

አሰራሩ በመንግስት የበጀት አጠቃቀምና እቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በኮንትራት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በእቅድ እንዳይመራና በዜጎችና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በኮንትራት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞች ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ ማድረግ ይገባል፡፡

1.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በዋና ግቢ ኮንትራት ሰራተኞችን ዘላቂነት ባለዉ የስራ መደብ በ2013 ዓ.ም በአንዳንድ የስራ ክፍሎች በተለያዩ ምክንያቶች ተቀጥረው እየሰሩ ይገኛሉ ፡፡ ሆኖም በአሁኑ ሰዓት በፌዴራል ኦዲት ባቀረቡልን ምክረ ሀሳብ ተቀብለን ዘላቂነት ባለዉ የስራ መደብ ላይ ኮንትራት ሰራተኞችን መቅጠር የምንቀንስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ በተጨማሪም ተቋሙ ያለውን የሰው ኃይል ክፍተት እና ፍላጎቱን ለማሟላት ለሚመለከተው አካል ለማስፈቀድ ጥረት እያደረግን ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች ቅጥር ዝውውር እና የደመወዝ ጭማሪ በጊዜያዊነት እንዲቆም በሚል በደብዳቤ በማሳወቀቻው እንደ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ወደፊት መንግስት እገዳውን እንዳነሳ አስፈቅደን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለኮንትራት ሠራተኞች የተከፈለው ተብሎ የቀረበው ሠራተኞች ደሞዝ የይማጅ ሆስፒታልን በመከራየታችንና ቀደም ሲል የይማጅ ሆስፒታል ሰራተኞች ቅጥራቸው በኮንትራት ስለነበር ሀይወት ፋና ሆስፒታል የይማጅ ሆስፒታል ሰራተኞችን በኮንትራት ተቀብሎ በኪራይ ውል መሰረት ደሞዝ እየከፈላቸው ስለሆነ ነው፡፡

ለዚህ ኪራዩ ሲቆም በአስፈላጊ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከተቀጠሩ ልዩ ሙያ ካላቸው ሠራተኞች ውጪ በኮንትራት ቅጥር የሚቀዩም መሆኑን በትህትና እንገልፃለን፡፡

1.2. ዘላቂነት በላቸው ስራዎች ላይ በቀን ሰራተኞች ማሰራትን በተመለከተ፤

1.2.1. ግኝት፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት

መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች (የተማሪዎች አገልግሎት ሰራተኞች፣የትራንስፖርትና ስምሪት ሰራተኞች፣ለጽዳትና ዉበት ሰራተኞች፣ጠቅላላ አገልግሎት፣ሾፌር እና የፋርማሲ ስቶር ክፍል ሰራተኞች)

**በዋና ግቢ በድምሩ ብር 5,638,470.04 (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)**

- **በሪፈራል ሆስፒታል በድምሩ ብር 743,900.00 (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)**

  በአጠቃላይ ድምር ብር 6,382,370.04 ቀጣይነት ባላቸው የሥራ ዘርፎች ቋሚ የሥራ መደብ ጥናት በማድረግ መዋቅር በሚኒስቴሩ በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሠራተኝነት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡፡በዋና ግቢ ለተከፈለዉ ብር 5,638,470.04 ሰራተኞቹ በሰዓቱ ገብተዉ ለመስራታቸዉ የሚቆጣጠሩበት የሰዓት መቆጣጠሪያ የፊርማ ሰነድ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ኃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሠራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ ታዉቋል፡፡

1.2.2. <u>ሥጋት፣</u>

አሰራሩ በመንግስት የበጀት አጠቃቀምና በእቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በዕቅድ እንዳይመራና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/ይገባል፡፡ በቀን ሰራተኛነት እየተከፈለ ያለው ክፍያም ሊቆም ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

#### 1.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋና ግቢ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን እና ከስፋቱ አንፃር በመዋቅር ደረጃ በተፈቀደልን የሰው ሀይል መደብ ስራዎችን ለማከናወን የማያስችል በመሆኑ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እና ስራዎችን ለማሳለጥ ሲባል የዩኒቨርስቲው የስራ አመራር አካላት መክሮበት ያለውን ክፍተት ለመቀነስ ሲባል በቀን ሰራተኛ እንደ አማራጭ ስለወሰድነው ነው፡፡ ተቋሙ ያለውን የሰው ኃይል ክፍተት እና ፍላጎቱን ለሚሟላት ለሚመለከተው አካል ለማስፈቀድ ጥረት እያደረግን ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች ቅጥር፣ የደመወዝ ጭማሪ እና ዝውውር በጊዜያዊነት እንዲቆም በሚል በደብዳቤ በማሳወቃቸው ፍላጎታችን ማስፈፅም አልተቻለም፡፡ ወደፊት መንግስት እገዳውን እንዳነሳ አስፈቅደን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

**በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** የቀን ሰራተኞችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲውና በሆስፒታሉ የሚገኘውን የተማሪዎች እና በሆስፒታሉ የሚገኙትን የበሽተኞች ቁጥር ብዛትን በተጨማሪም ሆስፒታሉ ተጨማሪ የህክምና ቦታ በመከራየቱ ያሉትን የሥራ ክፍተቶች በመደበኛ ሰራተኞች ማከናወን ስላልተቻለ እና ስራው እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ከመሆኑ አንፃር በቀን ሰራተኝነት እየተከፈላቸው እንዲሰሩ እና ወደፊት በሲቪል ሰርቪስ ጥያቄው ቀርቦ መደብ ለማፅደቅ እየተኬደበት መሆኑን በትህትና እንገልፃለን፡፡

### 1.3. የድህረ ምረቃ እና ፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን ፈተና ለፈተኑ የውስጥ እና የውጪ ፈታኝ ክፍያን በተመለከተ፣

#### 1.3.1. ግኝት፣

የፌዴራል ገንዘብ ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግስት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች ክፍያ መመሪያን ይመለከታል በሚል በቁጥር 2/አ/113/50 በቀን 20/7/2011 ባስተላለፈው መመሪያ ክፍል ሁለት በመንግስት በጀት ለሚሸፈኑ ክፍያዎች ተመን ቁጥር 5 መማር ማስተማር በተመለከተ ንዑስ ተ.ቁ 9.10 የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የመመረቂያ ፅሁፍ ለሚፈትኑ የውጭ ፈታኞች በመመረቂያ ፅሁፍ ብር 3,500.00 ለውስጥ ፈታኞች ብር 2,500.00 እንዲሁም ተ.ቁ11 የእንስሳት ህክምና የውስጥም ሆነ የውጭም ፈታኞች ለአንድ የመመሪያቂ

ፅሁፍ ብር 1,500.00 በመመሪያው ተገልጿል:: በተጨማሪም በመመሪያ መሰረት ለውጭ ፈታኞች በወጪ ደረጃ መሸፈን ያለባቸው የአየር ትኬት ወይም መኪና ምግብ መኝታ እንደሚሸፈን ይገልፃል፡፡እንዲሁም በተ.ቁ 12/13 የድህረ ምረቃ የሦስተኛ ድግሪ ተማሪዎች የጥናትና ምርምር ፈታኞች ለውስጥ 7,000.00 ለውጭ ፈታኞች 10,000.00 እንደሚከፈል መመሪያ ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት የመመሪያውን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

- በቀን 16/02/13 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ 512697 በሂሳብ መደብ 6417 ዩኒቨርሰቲው በእንስሳት ህክም CVM,DVM የተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፍ ለፈተኑ የውስጥም የውጭም ፈታኞች ለአንድ የመመረቂያ ፅሁፍ ብር 1,500.00 በመመሪያ መሰረት የተያዘ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዉ የስራ ግብርን ጨምሮ በወጪ መመዝገብ የነበረበት ብር 88,875.00 መሆን ሲገባው ዩኒቨርሰቲው በሰዓት ብር 1,500.00 በማስላት ታክስ ወጫቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 130,500.00 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 41,625.00 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 88,875.00 ላይ ስራ ግብር ብር 29,606.25 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 71,231.25 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ:: **(ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)**
- በቀን 12/05/2013 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ 240997 በሂሳብ መደብ 6417 ዩኒቨርሰቲው የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የመመሪቂያ ፅሁፍ ለሚፈትኑ የውስጥ ፈታኞች በመመረቂያ ፅሁፍ ብር 2,500.00 ለውጭ ፈታኞች ብር 3,500.00 የተቀመጠ ቢሆንም ዩኒቨርሰቲው ለ136 መምህራን የስራ ግብርን ጨምሮ በወጪ መመዝገብ የነበረበት ብር 424,200.00 መሆን ሲገባው ዩኒቨረሰቲው ከ5 ሰዓት እስከ 146 ሰዓት በሰዓት ብር 120.00 በማስላት ታክስ ወጫቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 637,701.00 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 213,201.26 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 424,200.00 ላይ ስራ ግብር ብር 146,970.00 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 360,171.26 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

➢ በቀን 15/05/2013 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ 932521 በሂሳብ መደብ 6417 በዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የመመረቂያ ፅሁፍ ለመፈተን የመጡ መምህራን በመመሪያ ከተፈቀድ ከአልጋ፣ የትራንስፖርት እና የምግብ መስተንግዶ ውጭ ለ133 ከተለያዩ ኮሌጅና ዲፓርትመንቶች ለመጡ እንግዶች በሚል በአዲስ አበባ የአበል ተመን መሰረት አድርጎ ለእያዳንዳቸው የ4ቀን አበል በማስብ በድምር ብር 396,028.00 ተከፈሎ ተገንቷል፡፡

➢ በቀን 21/04/2013 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ 37450 በሂሳብ መደብ 6417 በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የመመረቂያ ፅሁፍ ፈታና ለፈተኑ በሚል ለ133 መምህራን ብር 1,517,000.00 የተከፈለ ሲሆን የክፍያ ሁኔታው ዩኒቨርሲቲዉ የስራ ግብርን ጨምሮ በወጪ መመዝገብ የነበረበት ብር 1,061,900.00 መሆን ሲገባው ዩኒቨርሰቲው ታክስ ወጫቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 1,517,000.00 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 455,100.00 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 1,061,900.00 ላይ ስራ ግብር ብር 370,165.00 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 825,265.00 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፡፡

➢ በቀን 01/10/2013 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ 538425 በሂሳብ መደብ 6417 በድህረ ምረቃ እና የፒኤች ዲ ተማሪዎች ፕሮግራም የመመረቂያ ፅሁፍ ፈተና ለፈተኑ በሚል ለ95 መምህራን ብር 247,643.15 የተከፈለ ሲሆን የክፍያ ሁኔታው ዩኒቨርሲቲዉ የስራ ግብርን ጨምሮ በወጪ መመዝገብ የነበረበት ብር 214,800.00 መሆን ሲገባው ዩኒቨረሰቲው ታክስ ወጫቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 247,643.15 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 32,843.15 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 214,800.00 ላይ ስራ ግብር ብር 73,680.00 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 106,523.15 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፡፡

➢ በዋና ገቢ በውስጥ ገቢ ሂሳብ በቀን 16/02/13 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 37387 በዩኒቨርሰቲው postgraduate program የማስተርስ እና

የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎች የመመሪቂያ ፅሁፍ በተለያዩ ኮሌጆች ተማሪዎች ለፈተኑ መምህራን ለሚጀር አዳቫይዝር ለአንድ ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ብር 5000.00 ለአንድ ማስተርስ ተማሪ 2000 ለኮር አድቫይዘር ለአንድ ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ብር 2,000.00 ለኮር አድቫይዘር ለአንድ ማስተርስ ብር 1000.00 በማስብ ለ140 መምህራን ታክስን ጨምሮ ብር 1,028,500.00 መከፈል ሲገባው ዩኒቨርሰቲው ታክስ ወጪቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 1,582,274.53 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 553,774.00 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 1,028,500.00 ላይ ስራ ግብር ብር 358,475.00 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 912,249.00 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑና ክፍያዉም ከመደበኛ በጀት ላይ መከፈል ሲገባ ከዉስጥ ገቢ ላይ በመከፈሉ የመደበኛ ወጪ ያለአግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ መሆኑ፡፡

- በዋና ገቢ በውስጥ ገቢ ሂሳብ በቀን/02/13 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 37855 በሂሳብ መደብ 2617 በዩኒቨርሰቲው postgraduate program የማስተርስ እና የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎች የመመሪቂያ ፅሁፍ በተለያዩ ኮሌጆች ተማሪዎች ለፈተኑ መምህራን ለሚጀር አዳቫይዝር ለአንድ ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ብር 5000.00 ለአንድ ማስተርስ ተማሪ 2000 ለኮር አድቫይዘር ለአንድ ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ብር 1,500,00 2,000.00/2500.00 ለኮር አድቫይዘር ለአንድ ማስተርስ ብር 1000.00 በማስብ ለ58 መምህራን ታክስን ጨምሮ ብር 168,000.00 መከፈለ ሲገባው ዩኒቨረሰቲው ታክስ ወጪቸውን በመሸፈን ተከፋዩ እንዳይነካ በሚል ብር 258,461.43 አድርጎ ክፍሎ የመዘገበ ሲሆን በልዩነት ብር 90,461.43 አላግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑና መከፈል ከነበረበት ብር 168,000.00 ላይ ስራ ግብር ብር 57,300.00 ሳይቀነስ በመከፈሉ በድምሩ ብር 147,761.43 ከደንብና መመሪያ ዉጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑክፍያዉም ከመደበኛ በጀት ላይ መከፈል ሲገባ ከዉስጥ ገቢ ላይ በመከፈሉ የመደበኛ ወጪ ያለአግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ መሆኑ፡፡

1.3.2. **ሥጋት፣**

- ዩኒቨርሰቲው የመምህራን ክፍያዎች  በደንብና መመሪያ ከተፈቀደው ወጪ ክፍያ የሚከፍል ከሆነ የህግ ጥሰት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ማናቸውም ግለሰብ ከተከፈለው ክፍያ ላይ ተገቢው ታክስ መቆርጥ የሚገበው ሂሳብ ሳይቆረጥ በተቋሙ የሚሸፈን ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት እና ለህግ ጥሰት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ሰዓት ክፍያ መከፈል ካለበትም የሚመለከተው መ/ቤትን በማስፈቀድ እና ሲፈቀድ ብቻ መሆን ይገባል፡፡

1.3.3. **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ዩኒቨርሰቲው ማናቸውም የመምህራን ክፍያ ከደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ መክፈል በህግ የሚያስጠይቅ እንደሆነ ተረድቶ  ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡ ስለዚህ መከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለው የመምህራን ክፍያ፣ አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል እና ከግለሰቦች መቀነስ የነበረበት ታክስ በተቋሙ የተሸፈነው ታክስ ተገቢነት እንደሌላቸው ታውቆ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.3.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

ዋና ግቢ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ዩኒቨርሲቲዎች ሐገሪቱ እየተከተለች ያለውን ለውጥ ሊመራና ሊያሳካ የሚችል ዜጋ በታቀደው መሰረት ከማፍራት አንጻር የተጣለባቸው ከፍተኛ ኃሊፊነት የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት በማስጠበቅ ኢኮኖሚው የሚፈልገውን ቁጥር ብቁ የተማረ ዜጋ በሚፈልገው የትምህርት መስክ የሰለጠነ እና ተፎካካሪ የሆነ ዜጋ ማፍራት እና ብሎም የማህበረሰብን ችግር መሰረት ያደረገ ጥናትና ምርምርን በማካሄዱ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና እውቀቶችን በማፍለቅ ወደማህበረሰቡ በማሸጋገር የማህበረሰቡን ችግር መፍታትና ማገዝ ነው፡፡ ስለዚህ የተሰጠንን ሀገራዊ ተልእኮ ለማሳካት ነባርና በቂ እውቀት  ያላቸውን መምህራን በመላው ሀገሪቷ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ብሎም ከሀገር ውጪ እየፈለግን እየጋበዝን ዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት በዘርፉ በሰለጠኑ መምህራን እያሰለጠንን በጣም ውስንና ለመምህራኑ በቂ ነው ተብሎ ሊወራ በማይችልበት መልኩ አገልግሎት ለሰጡበት

ጉልበታቸው/እውቀታቸው ላፍሰሱበት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን ክፍያ መክፈልና ማሰናበት ስላለበት ክፍያው እንዲከፈላቸው ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ያለንበት አካባቢ ወጣ ያለ በመሆኑ መምህራን ወደ አካባቢው መጠው አገልግሎት ለመሰጠት ፍላጎት ያነሰ በመሆኑ እነሱን ለማበረታታት በስራ አመራር አካላት ታምኖበት እንዲከፈል የተደረገ ነው፡፡

## 1.4. <u>ለዉሎ አበል ክፍያዉ ተገቢዉ ደጋፊ ሰነድ ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ በተመለከተ፣</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ዉሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል ሶስት አንቀጽ 9/1 ላይ ማንኛዉም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታ ዉጭ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ዉሎ አበል መጠየቂያ፣መክፊያና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለዉ ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል ይላል። በዚህ መሰረት የመመሪያውን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፦

- ☞ በዋና ግቢ ለአስተዳደር እና ለአካዳሚክ ባለሙያዎች የተከፈሉ የውሎ አበል ክፍያዎች የጉዞ አላማ ሳይገለፅ እና ሳይታወቅ ብር 746,661.00 የተከፈለ መሆኑን **(ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)**
- ☞ በድምሩ ብር 206,628.50 ውሎ አበሉን የጠየቀው ክፍል እና የውሎ አበል የተሞላበት ቅፅ ሳይኖር ዉሎ አበል የተከፈለ መሆኑን፣ **(ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)**

በድምሩ ብር 953,289.50 ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ (የዉሎ አበል የጉዞ አላማ ሳይገለጽ እና የዉሎ አበል ቅጽ ሳይኖር) በመክፈሉ ለተከፈለው ክፍያ ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

### 1.4.1. <u>ሥጋት፣</u>

ማናቸውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ተገቢው ማስረጃ ሳይረጋገጥ የሚከፈል ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኝነት ላያመለክት ይችላል። እንዲሁም ዉሎ አበል ከመክፈላቸው በፊት ለዉሎ አበል ተገቢው ማስረጃ(ቅጽ) ሳይቀርብ ክፍያ የሚከናወን ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

1.4.2. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ዩኒቨርስቲው ማናቸውንም ክፍያ ከመክፈሉ አስቀድሞ ማስረጃዎች መሟላታቸውንና ትክክለኛነታቸውን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ ሌሎች ለተከፈሉት ክፍያዎች በአግባብ ክትትል እየተደረገ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

1.4.3. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

በዋና ግቢ የጉዞ አላማ ሳይገለፅ እና ሳይታወቅ ለሚለው እና ውሎ አበሉን የጠየቀው ክፍልና የውሎ አበል የተሞላበት ቅፅ ሳይኖ በሚል ለቀረበው ስራው የተሰራ ሲሆን ነገርግን ከስራ ብዛት የተነሳ ባለሙያዎች መረጃውን በትክክል መሙላቱን መያያዙን አለማስተዋል የተነሳ የተፈጠረውን ስህተተ ሲሆን ወደፊት የሚታረም ሆኖ እንዲህ አይነት ክፍተቶች እንዳይከሰቱ፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ከፍተኛ ክትትል የምናደርግ መሆኑን እንሳውቃለን ስህተቶችን በድጋሜ የሚፈፅም ባለሙያ ከተገኘ አስተዳደራዊ እርምጃ የምንወስድ መሆኑ በአክብሮት እናሳውቃለን ፡፡

1.5. **ከፕሮጀክት መክፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ የቤት ኪራይ በተመለከተ፣**

1.5.1. **ግኝት፣**

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ክፍል ሦስት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመደበኛ በጀት የሚከፈል ክፍያዎች ለመደበኛ ስራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በዋና ግቢ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱን ለመከታተል የመጡ የወጪ ሀገር ዜጋ በሐረር ከተማ ውስጥ የሚገኘውን የአቶ ብሩ ነጋ ያሲማ መኖሪያ ቤት ተከራይተው ለግለሰቡ በወር

30,000.00 በማሰብ የዘጠኝ ወር ብር 270,000.00 ከደንብና መመሪያ ወጪ ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ በመገኘቱ የመደበኛ ወጪ ያለአግባብ በዚህ ገንዘብ መጠን ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርጎታል። በተጨማሪም ለክፍያዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።**(ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)**

1.5.2. **ሥጋት፣**

መንግስት በጀት ለታለመለት አላማ ላይውል ይችላል፡፡

1.5.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው በበጀት አመቱ ከፌደራል መንግስት የሚበጀትለት በጀት ለታለመለት አላማ ሊውል ይገባል፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክት ለመከታተል ለመጡ የወጪ ሀገር ዜጋ የቤት ኪራይ ክፍያ ከበጀት መክፈል አግባብነት እንደሌለው ታውቆ ከፕሮጀክት ሂሳብ ተቀንሶ ወደ መደበኛ በጀት ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ወደፊት መሰል ችግሮች እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.5.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

በዋና ግቢ የቤት ኪራዩን በተመለከተ ተቋማችን የምርምር ተቋም እንደሆነ መጠን ጥናት እና ምርምርን መሰረት ባደረገ መልኩ ለሀገር ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን ተጻጽሮ በማምጣት ዩኒቨርስቲውን ውጤታማ አድርጎታል፡፡ ሆኖም ወደ ሀገር ውስጥ ከመጡ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንድን ለመከታተል የመጡ የውጪ ዜጋ በሆቴል ለማስቀመጥ ወጪው ከፍተኛ ስለሆነ እና የቆይታቸው ጊዜ ረዝም ያለ ስለሆነ የግለሰብ ቤት ተከራይተን የመንግስት ወጪ ለመቀነስ ተችሏል፡፡

1.5.5. **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

ግኝቱ በሆቴል ይቀመጡ ሳይሆን ለፕሮጀክት ሥራ ከመደበኛ በጀት መክፈል የለበትም ነዉ፡፡

1.6. **ያልቀረበ የንብረት ገቢ ደረሰኝ በተመለከተ፣**

1.6.1. **ግኝት፣**

ፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ዕቃዉ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ/ሞዴል 19/ መያያዝ እንዳለበት ይገልፃል።ይሁን

እንጂ ዩኒቨርሲቲዉ በዋና ግቢ በግቢው ውስጥ ላሉ ተሽከርካሪዎች በተለያየ ጊዜ ወደ ካምፓኒዎች ወስዶ ሲያስጠግን ተቀየረ ለተባለው የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ብር 865,236.20 ክፍያ ሲከናውን የአሮጌ ተመላሽ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልቀረበ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል ፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)**

1.6.2. ***ሥጋት፣***

- ዩኒቨርስቲው ክፍያ ከመክፈሉ በፊት ተገቢው ማስረጃ ሳይረጋገጥ የሚከፍል ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነትና ለመዝበራ ሊጋለጥ ይችላሉ
- ዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ከተጠገኑ በኃላ የአሮጌ ዕቃዎች መለዋወጫ የተመላሽ የንብረት ደረሰኝ ተቆርጦለት ሳይረጋገጥ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ ክፍያውን አመኔታ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

1.6.3. **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

ዩኒቨርሲቲው በእርዳታም ሆነ በግዢ ላመጣቸው ዕቃዎች ሂሳብ ሲወራረድ በደንብና መመሪያ መሰረት ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል ፡፡ ስለዚህ መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች ሊቀርቡ ይገባል፡፡

1.6.4. ***<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>***

ከዛሬ ጥር 23 /2014 ዓ.ም ጀምሮ ይህንን በፌደራል መንግስት በተሰጠው መመሪያ መሰረት ማንኛውንም የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪች ጥገና ወደ ካምፓኒዎች ሲላክ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ጥገናዎች ሲከናወኑ ተቀያሪ ለተባሉት ተሽከርካሪዎች የአሮጌ ዕቃዎች ተመላሽ ንብረት ገቢ ደረሰኝ ከክፍያ ሰነድ ጋር እንደቀርብ በማድረግ የእርማት እርምጃ እንወስዳለን፡፡

## 1.7. <u>የተሽከርካሪ እና የጀንሬተር ጥገና ዝርዝር የስራ ማስረጃ አለመቅረብን መለከተ፤</u>

1.7.1. **<u>ግኝት፣</u>**

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በመደበኛ እና በካፒታል በጀት የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ክፍያዎች በተመለከተ በተራ ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል:: በዚህ መሰረት የወጪውን ትክክለኘነት ለማጣራት ኦዲት ሲደርግ፡-

☞ ዩኒቨርስቲው በግቢው ውስጥ የሚገኝ የተሽርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-14847ኢት ፒክአፕ ሞተር ሰርቪስ፣ እግር እና ኤሌክትሪክ በብር

420,000.00፣የሰሌዳ ቁጥር-4-17365 አውቶብስ ተሸከርካሪ በብር 402,990.70 ዝርዝር የጥገና ሥራ ማስረጃ ሳይኖር ሰርቪስ ተደርጎ የአገልግሎት ወጪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

☞ በዋና ግቢ የቦይለር ጥገና በሚል ብር 315,000.00 እንዲሁም ዋና ግቢ MTV1050 KVA የጀኔሬተርና ራሬ ውሃ ብርካ ያለው ውሃ ማስራጫ ጥገና ብር 500,000.00 በድምር ብር 815,000.00 ዝርዝር የጥገና ሥራ ማስረጃ ሳይኖረው ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል።**(ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)**

በድምሩ ብር 1,637,990.70 ዝርዝር የጥገና ሥራ ማስረጃ ሳይኖረው የጥገና ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል።

1.7.2. **ሥጋት፣**

ከክፍያዎች ጋር ተገቢው ዝርዝር ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ የክፍያውን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

1.7.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ማናቸውንም የመንግስት ክፍያዎች ከመከነውናቸው በፊት ግዥርውንም ሆነ የአገልግሎቱ ክፍዎች በትክክል ስለመሰራቱ ተራጋግጦ እና ዝርዝር ማስረጃዎች ሲቀርቡ ብቻ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.7.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

ጥገናው ስለመሠራቱ ደግሞ የክፍሉ ባለሙያዎች ካረጋገጡ በኋላ ነው ክፍያው የተፈፀመው።

## 1.8. በትክክለኛ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ በተመለከተ፤

1.8.1. **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 7 ፊዴል ሀ የመንግስት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸዉን በጀት በሥራ ክፍል ወይም በፕሮጀክት፣በፋይናንስ ምንጭ እና በየወጪ የሂሳብ መደቡ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ከፍተዉ እንቅስቃሴዉን መመዝገብና መቆጣጠር እንዳለባቸው ይገልጻል። የፌዴራል የመንግስት የሂሳብ አመዘጋገብና አወቃቀር ስርዓት 1999 በግልፅ ተቀምጧል። በዚህ መሰረት ማናቸውም የመንግስት ሂሳቦች መንግስት ባስቀመጠው መሠረት ተግባራዊ መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት የሚውሉ ግዥዎች ፊፀም ክፍያ ሲከፍል በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ወጪ መደረግ ሲገባው በትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ብር 2,614,736.00 መኖሩን በኦዲት ተረጋግጧል።**(ለዝርዝሩ አባሪ 10 ተያይዟል)**

1.8.2. **ሥጋት፣**

ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ አርዕስት ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል።በተጨማሪም በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል።

1.8.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። በተጨማሪ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርስ በመሆኑ ወጪዎች የሚመዘገቡት በትክክለኛው የበጀት አርዕስታቸው ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

1.8.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

ሂሳብ መደብን በተመለከተ የተገኘው የኦዲት ግኝት ምዝገባው ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል በአሁኑ ሰዓት ሂሳብ የተዘጋ በመሆኑ ማስተካከል ስለማይቻል በቀጣይ ከዚህ ስህተት በመማር የወጪ ሂሳብ መደቦችን ጠብቀን በጥንቃቄ የምንሰራ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

## 1.9. የሚመለከተዉ አካል ሳያስፈቅድ የሞተር ሳይክል ግዥ በተመለከተ

1.9.1. **ግኝት፣**

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ሐምሌ 2002ዓ.ም ተ.ቁ 4.4 የተሽከርካሪ እና የመለዋወጫዎች ግዥ ንዑስ ቁጥር 4.1 .1.5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊ አስቸኳይ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት የተሽከርካሪ ግዥ መዘግየቱ በመስሪያ ቤቱ ስራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን ሲታምንበት ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አቅርቦ ሲፈቀድለት ለዝርዝር አፈጻጸሙ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣንን ሀሳብ በመጠየቅ ግዥ በራሱ ሊፈፅም እንደሚችል በግልፅ ተቀምጧል። በዚህ መሰረት የመመሪያውን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርስቲው የሞተር ብስክሌቶች ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፍቃድ ሳያገኝ በተለያዩ ጊዜ በዋጋ ማውዳደሪያ የግዥ ዘዴ

በመጠቀም በብር 679,025.00 የሞተር ብስክሌቶችን ግዥ ፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 11 ተያይዟል)**

1.9.2. ***ሥጋት፣***

ዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሳይፈቀድለት መግዛት የህግ ጥሰት ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.9.3. ***የማሻሻያ ሀሳብ፣***

ዩኒቨርሲቲው የተሽከርካሪ ግዥ በመመሪያዉ መሰረት የሚመለከተዉን አካል በማስፈቀድ ግዥዉን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

1.9.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ፣***

የኦዲት ባለሙያዎች እንደገለፁት ተሽከርካሪ የመግዛት ሥልጣን የተሰጠው "የመንግስት ግዥ አገልግሎት" ሲሆን ሌሎች የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪውን ግዥ መግዛት ያለባቸው መሆኑን ቢታመንበትም የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ግዥውን ሲፈቅድ ለመንግስት ግዥ አገልግሎት ደብዳቤ በመፃፍ ማስፈቀድ ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ኮሮና ቫይረስ በተከሰተበት ወቅት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በምስራቁ የአገራችን ክፍል ላሉት አካባቢዎች ማለትም ለምሥራቅ ሐረርጌ ዞን፣ ለሐረሪ ክልል፣ ለድሬዳዋ አስተዳደር እና ለሱማሌ ክልል እንደ ኳራንታይን ጣቢያ ማለት የተጠረጠሩ ሰዎች እስኪጣራ ድረስ የሚቆዩበትና በCOVID-19 መያዛቸው በግልፅ ለታወቁት እንደ መታከሚያ ቦታነት እንዲያገለግል በመወሰኑ የኳራንታይን ሕክምና ሥራውን የሚሰሩ ሰራተኞች ከዋናው ግቢ እስከ ግንደጀ (ኳራንታይን ቦታ) ከዋናው ግቢ ሐረማያ ሆስፒታል እና ሐረር ሕይወት ፋና ስፔሻያላይዝ ሆስፒታል እና ድሬዳዋ ድረስ ለመመላለስ በአስቸኳይ የሞተር ሳይክሎች በማስፈለጋቸውና ከሚመለከታቸው አካል ፍቃድ ለማግኘት የማይቻልበትና የማይታሰብበት ወቅት በመሆኑ በበላይ አመራሩ ፍቃድ ነው የሞተር ሳይክሎች ግዥ የተፈፀመው፡፡ለወደፊቱ ግን ኮሮና ቫይረስ በተከሰተበት ወቅት ያጋጠመን እንቅስቃሴን ሁሉ የሚከሰተውን ሁኔታም ሊያጋጥመን ስለማይችል የኦዲት ባለሙያዎች በሰጡት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድልን፡፡

## 1.10. ቀጥታ ከአንድ አቅራቢ የተፈጸመ ግዥን በተመለከተ፣

### 1.10.1. ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 በወጣው ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት የፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ይላል፡፡ በዚህም መሠረት የዩኒቨርሲቲው የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡- ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል ዳቦ በብር 716,525.00 ግዥ ያለጨረታ (ያለዉድድር) በቀጥታ ከአንድ ድርጅት ግዥዉ የተፈፀመ መሆኑን ታዉቋል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 12 ተያይዟል)**

### 1.10.2. ሥጋት፣

ግዥ በመመሪውያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብም ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

### 1.10.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም የእቃና የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጽም በመንግስት የግዥ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሊፈጽም ይገባል፡፡
- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መ/ቤቱ የሚፈፅመው ግዥ በዋጋ ውድድር መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው የግዥ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ

እንዲሁም ለተቋሙ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር በቀጥታ ግዥ በተደጋጋሚ መፈፀም የተሻለ ዋጋ በማግኘት ረገድ የዩኒቨርሲቲውን ጥቅም የሚያሳጣ በመሆኑ አሠራሩ ሊስተካከል ይገባል፡፡

1.10.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በዋና ግቢ ለዩኒቨርስቲው ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል ዳቦ በቀጥታ ግዥ ተፈፀመ ለተባለው ባለፉት ዓመታት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪ ቀለብ ዳቦ ለመግዛት ጨረታ ባወጣባቸው ጊዜ በአካባቢያችን ሐረርና ድሬደዋ ከተማን ጨምሮ ከድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ ውጪ በጨረታ ላይ ሲወዳደር የነበረ አንድም ተጫራች ስለአልነበረ የድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ የዳቦ ዋጋን እንደፈለጉ ከፍ ሲያደርጉ የነበረ ሲሆን ለምሳሌ በአንድ ዓመት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በብር 1.25 ሲገዛ የነበረውን ባለ 120 ግራም ዳቦ የድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ በብር 2.25 ሲሸጥብን የነበረ ከመሆኑም በላይ በዚህም በጀት ዓመት መንግስት ገበያን ለማረጋጋት ከውጪ በድጎማ ሲያስገባ የነበረው ስንዴ በመቅረቱ በብር 2.00 ሲቀርብልን የነበረውን ባለ 120 ግራም ዳቦ ብር 5.30 ካልከፈላችሁኝ በማለቱ በአካባቢያችችን በአዲስ የተከፈተውን ስንቃብዝ ብር 5.30 ካልከፈላችሁኝ አላቀርብም ብሎ የነበረውን ዳቦ በብር 4.50 አብረው እንዲያቀርቡ ማድረግ ችለናልና በዚሁ ምክንያት የመንግስትን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የሆነ ነው፡፡ ለወደፊቱ ግን የፌዴራል ዋና ኦዲተር ባለሙያዎች በሰጡን አስተያየት መሠረት ግዥዎች የመግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት ብቻ እንዲገዙ እናደርጋለን፡፡

## 1.11. <u>የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተገቢው ስፔስፍኬሽን ሳይወጣለት የተፈጸመ ግዥን በተመለከተ፤</u>

1.11.1. <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር ተ.ቁ (2) ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መሰጠቱን አግባብ ባለው ሠራተኛ ተረጋግጦ ክፍያው ሊፈጸም እንደሚገባ በተጨማሪም ተ.ቁ (4) አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች /Technical

committee/ የጹሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ቢያመለክትም:-**በሪፈራል ሆስፒታል ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከዉስጥ ገቢ ሂሳብ በድምሩ በብር 510,583.50 የተገዙ ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተገቢው የስፔስፍኬሽን ሳይወጣለት ግዥ ተፈጽሞ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል:: **(ለዝርዝሩ አባሪ 13 ተያይዟል)**

1.11.2. ***ሥጋት፣***

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ወይንም አገልግሎት መገኘቱን ተረጋግጦ ክፍያ ካልተፈጸመ ዩኒቨርሲቲው ከገዛው ዕቃ ሊያገኝ ያቀደውን ወይም አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል:: ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ ሊፈጸም ይችላል::

1.11.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

- ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ እንደ አስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን በህሪይ የሚያሟላ መሆኑን የሚረጋገጥበት አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል:: ወደፊት መሰል ችግሮች እንዳይፈጠሩ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል::

1.11.4. ***ሥራ አመራሩ ምላሽ፣***

በሪፈራል ሆስፒታል ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እስፔስፊኬሽን በተመለከተ የግዢ ጠያቂ ክፍሉ በግዢ መጠይቅ ላይ ባሠፈረው መጠነኛ የእቃ መግለጭ መሠረት በማድረግ እና በክፍሉ ባለሞያ በመታገዝ የተጠቀሱት እቃዎች የተገዙ ናቸው:: ነገር ግን የእቃው መግለጫ ሳይጠቀስ ያልተገዙ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ እንዲገነዘብልን በማክበር እንጠይቃለን::

## 1.12. የንግድ ምልክት (ብራንድ) በመጥቀስ የተገዛ የተሽከርካሪ ጎማን በተመለከተ

1.12.1. **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀፅ 16.5 (ሠ) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጭ ማመልከት (መጥቀስ) እንደሌለበት ይገልጻል :: ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲዉ:-

- **በዋና ግቢ** የሀረማያ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ ጎማ፣ታብሌት እና ላፕቶፕ ለመግዛት በተለያዩ ጊዜ የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ሲያወጣ የአምራቾችን

የንግድ ምልክት (ብራንድ) በመጥቀስ ብር 437,950.00 ግዥ እንደፈፀመ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል ። **(ለዝርዝሩ አባሪ 14 ተያይዟል)**

- **ዩኒቨርስቲ ሐረማያ ጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ** የህይወት ፋና ሆስፒታል በውስጥ ገቢ ሂሳብ በቀን 20/4/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 150280 ሐርረ ከሚገኘዉ ከኢሉ-ኤት ትሬዲንግ DELL ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች እና HP ፕሪንተሮች በማለት በዋጋ ማቅረቢያዉ(ፕርፎርማዉ ለመግዛት በተለያዩ ጊዜ የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ሲያወጣ የአምራቾችን የንግድ ምልክት (ብራንድ) በመጥቀስ ብር 170,775.00 ግዥ እንደፈፀመ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል።

**1.12.2. *ሥጋት፣***

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም ፣ የመንግስትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል።

**1.12.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

ግዥዎች በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መከናወን አለባቸው።

**1.12.4. *የሥራ አመራሩ ምላሽ፣***

- ዋና ገቢ በተመለከተ የንግድ ምልክት (ብራንድ) በመጥቀስ የተገዙ የተሽከርካሪ ጎማን የተመለከተ፣ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የፌዴራል የመንግስት ግዥ መመሪያ በሚያዘው መሠረት በሚፈፅማቸው የግዥ ሂደት ውስጥ የተወሰኑ ወገኖችን (አቅራቢዎችን) ፊበር አድርጎ ሌሎችን የሚያገል ግዥ እንደሚፈፀም የጨረታ ሰነዶች ሲዘጋጁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲዘጋጅና ግዥዎች እንዲፈፀሙ እያደረግን እንገኛለን። ነገር ግን የኦዲት ባለሙያዎች በጠቀሱት መሠረት የኘሮፎርማ ግዥ በሚፈፀምበት ወቅት ቀጥታ ግዥ ጠያቂ ክፍሎች በግዥ መጠይቅ ላይ በሞሉት መሠረት በስህተት ማስተካከያ ሳይደረግ የንግድ ምልክትን በመጥቀስ የተፈፀሙ ግዥዎች ናቸው።ለወደፊቱ የኦዲት ባለሙያዎች በሰጡት አስተያየት መሠረት በኘሮፎርማ የሚፈፀሙ ግዥዎችንም ቢሆን የንግድ ምልክቶች (ብራንዶች) ሳይጠቀሱ የሚፈለገውን

ጥራት ዝርዝር ስፔስፊኬሽን በማዘጋጀት ሁሉንም አቅራቢዎች በማያገል ሁኔታ ግዥ እንዲፈፀም እናደርጋለን፡፡

* ዩኒቨርስቲ ሐረማያ ጤናና ህክምና ሰይንስ ኮሌጅ የህይወት ፋና ሆስፒታል በማንኛውም የግዢ መንገዶች ብራንድ ጠቅሶ መግዛት የማይቻል መሆኑን ይገለፃል፡፡ ነገር ግን ከጠያቂ ክፍሎች ጥያቄና ፍላጎት በመነሳት እና ለተወዳዳሪ አካላት ግልፅ ለማድረግ በማሰብ እንዲሁም ግዢው ከተከናወነ በኋላ ጠያቂ ክፍሎች በእውቀት ማነስ ይሁን በሌላ ምክንያት ከጠየቁት ውጪ ከሆነ እቃው ጥራቱን ያልጠበቀ መስሎ ስለሚታያቸው እቃውን ያለመረከብ ፍላጎቶች ብዙ ጊዜ ስለሚታዩ እነዚህን ክፍተቶች ለማቻቻል በሚል ህጉ ባይፈቅድም ብራንዶችን ለመጥቀስ ስለምንገደድ እንጂ ሌሎችን ለመጥቀም እንዳልሆነ እንዲታወቅልን በትህትና እንገልፃለን፡፡

## 1.13. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሳያቀርቡ ግዥ ላይ ተወዳድሮ ያሸነፉ ድርጅቶች በተመለከተ፣</u>

### 1.13.1. <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 33/2 ፊደል ሀ እስከ ሠ በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር የተገለጸ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ከተለያዩ ድርጅቶች ለተገዙ ዕቃዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቀረቡ ድርጅቶችን በማወዳደርና አሸናፊ አድርጎ በመምረጥ በድምር ብር 350,267.91 ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡**(ለዝርዝሩ አባሪ 15 ተያይዟል)**

### 1.13.2. <u>ሥጋት፣</u>

የግብር ከፋይና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቀረቡ ድርጅቶችን ማወዳደርና አሸናፊ አድርጎ መምረጥ ህገ-ወጥ አቅራቢዎችን የሚያበረታታ እና ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

### 1.13.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው አቅራቢዎችን ሲያወዳድር ህጉ የሚፈቅደውን ሁሉ ማስረጃዎች ማለትም የግብር ከፋይ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡በመሆኑም የግብር ከፋይ እና የተጨማሪ

እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ባቀረቡ እንዲሁም ሳያቀርቡ ውድድር እንዲወዳደሩ እና በአሸናፊነት ተመርጠው እቃዎችን እንዲያቀርቡ ለምን እንደተደረገ ተጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

<u>**የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**</u>

የግብር ከፋይና ተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባን በተመለከተ ድርጅቶቹ ይኸው ሰርተፍኬት ያላቸው ሲሆን በስራ መደራረብ ምክንያት እንዲሁም በወቅቱ የኮቪድ በሽታ ስርጭትን ለመከላከል በነበረው ጥድፊያ ሳይታዩ የተዘለሉ ስለሆነ ወደፊት የምናስተካክል መሆኑን የኦዲት ቡድኑ እንዲያውቅልን ስንል በትህትና እንጠይቃለን፡፡

### 1.14. <u>ግዥዉን በማዕቀፍ ግዢ ባለማከናወኑ ምክንያት መንግስት ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ በተመለከተ</u>

#### 1.14.1. <u>ግኝት፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 61 ን.አ. 1) የመንግስት መ/ቤቶች ላላቸዉ ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት ወይም አንድ የመንግስት መ/ቤት በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ በተደጋገሚ ለሚኖረዉ የግዥ ፍላጎት ግዥዉን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም እንደሚቻል መገለፁን፡፡ እንዲሁም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በቀን 16/07/2011 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ/ሰሀ/04/716/786 በተፃፈ ደብዳቤ የ2011-2013 በጀት አመት የጋራ መጠቀምያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ስምምነት የግዢ አቅራቢ ድርጅቶችን አሳዉቋል፡፡ በዚህም መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

- **በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በውስጥ ገቢ ሂሳብ** ኮሌጁ የተለያዩ እቃዎች ከግዢ ኤጀንሲ በተላከዉ የማዕቀፍ ግዢ መሰረት ግዢ መፈፀም ሲገባ አላግባብ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዢ በመፈፀሙ ምክንያት ዩኒቨርሲቲዉ ብር 148,184.67 ለተጨማሪ ወጪ ተዳርጎ ተገኝቷል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 16 ተያይዟል)**
- **በሆስፒታሉ የመደበኛ በጀት** ላይ የ2013 በጀት ዓመት የተገዙ የፅህፈት መሳሪያዎች በማዕቀፍ ግዥ መፈፀም ሲገባ አላግባብ በዋጋ

ማወዳደሪያ ግዢ በመፈፀሙ ምክንያት ሆስፒታሉ ብር 361,158.00 ለተጨማሪ ወጪ ተዳርጓል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 27 ተያይዟል)**

በአጠቃላይ በማዕቀፍ ግዥ መፈፀም ሲገባ አላግባብ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዢ በመፈፀሙ ምክንያት በድምሩ ብር 509,342.67 ያለአግባብ መንግስት ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡

1.14.2. ***ሥጋት፣***

ዩኒቨርሲቲዉ ከላይ በተገለፀዉ መሰረት ግዥዉን በማዕቀፍ ግዢ ባለማከናወኑ ምክንያት ከላይ የተገለፀዉ የገንዘብ መጠን እንዲባክን ተደርጓል፤ ይህም የዩኒቨርሲቲዉ የበጀት አጠቃቀም ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባና ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት ነዉ፡፡ (በማዕቀፍ ስምምነት መገዛት ያለባቸዉ ዕቃዎች በዋጋ ማወዳደሪያና በግልፅ ጨረታ መግዛት የመንግስትን ዉስን ሀብት ለብክነት ሊዳሪግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ግዥዎችን በጋራ መፈፀም ሊድን የሚችለዉን ወጪ ሊያሳጣ ይችላል)፡፡

1.14.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲዉ የመንግስትን የግዢ አዋጅና መመርያን መሰረት በማድረግ ግዢዎችን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢዉን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በማዕቀፍ ግዢ ያልተካተቱ፤ ታቅደዉ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎቶችን በተመለከተም ግዥን በማቀድ በዩኒቨርሲቲዉ ደረጃ ግልፅ ጨረታ በማዉጣት ግዢዎች መፈፀም አለበት፡፡ (በግዥ ኤጀንሲ በኩል በማዕቀፍ ስምምነት መገዛት የለባቸዉ ዕቃዎች ስምምነት መሠረት መገዛት ያለባቸዉ ሲሆን፤አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ግዥ ኤጀንሲ በማስፈቀድ ሊፈፀም ይገባል፡፡በቀጣይም በማዕቀፍ ሊፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት በማጣራት ተገቢዉን ማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል)፡፡

1.14.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

- በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከላይ የተጠቀሱት ግዢዎች በማዕቀፍ ግዢ ውስጥ ያሉ ቢሆኑም ሆስፒታሉ ሪፈራል ሆስፒታል በመሆኑ ብዙ አገልግሎቶችን ለታካሚዎች የሚሰጥ እንደመሆኑ መጠን የማዕቀፍ ግዢዎች የሚዘገዩና በሚፈለገው ፍጥነት የማይቀርቡ በመሆናቸው

እንዲሁም ካለው የሆስፒታሉ ነባራዊ የእድገት ደረጃ አንፃር የህክምናው እና የአስተዳደር ስራው ላይ ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግ የተከናወኑ ግዢዎች መሆናቸውን ከዚህም በላይ የማዕቀፍ ግዢ አቅራቢዎች አቅርቦታቸው የሌለ በመሆኑና እንዲሁም ግዢዎችን እንድናከናውን ከበላይ አካል የተፈቀደ መሆኑን በትህትና እንገልፃለን፡፡

## 2. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

### 2.1. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

#### 2.1.1. ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ 7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም ሰኔ 30/2013 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ከሚታይ ውስጥ በጊዜ ገደቡ መወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ የቆየ

1. ከአንድ አመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ብር 20,140,143.44
2. ከአምስ ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ ብር **36,320,720.73**፣

በድምሩ ብር **56,460,864.17** በደንቡ መሰረት ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰብ) በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ **(ዝርዝሩ በአባሪ 18 ተያይዟል)**

#### 2.1.2. ሥጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

#### 2.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም

የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

- ወደ ወጪነት መቀየር ያለበት ሂሳብ በወቅቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጠንካራ የውስጥ አሰራር ሊዘረጋ እና ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ተፈጥሮ በሂሳብ አያያዝ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ተገቢ ማስረጃ በመያዝ መሰብሰብና ወደ ወጪነት መቀየር የማይችሉትን ደግሞ ለሂሳብ መዝገቡ እርምት እርምጃ በህጉ መሰረት ሊወሰድ ይገባል፡፡
- በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ለግዥ ወጪ የተደረጉ ቅድመ ክፍያዎች በሰባት የስራ ቀናት እንዲሁም ለውሎ አበል ክፍያ ወጪ የተደረጉ ቅድሚያ ክፍያዎች ለመስክ ስራ የወጣው ሰራተኛ በተመለሰ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ የሚወራረድበትን ሥርዓት እና ለግዥ ሰራተኞች የሚሰጡ ቅድመ ክፍያዎች በቅድሚያ የተሰጠ ክፍያ ሳይወራረድ ተጨማሪ ሰነድ እንዳይሰጥ ጥንቃቄ በማድረግ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለበርካታ ጊዜ እንዳይቆዩ መደረግ አለበት፡፡

2.1.4. <u>**የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**</u>

ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳቡ ከሚመለከታቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች በወቅቱ መሰብሰብ የሚገባቸው እንዲሰበሰቡ፣ ወደ ወጪነት መቀየር ያለበት ሂሳብ በወቅቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጠንካራ የውስጥ አሰራር ቁጥጥር ዘርግቶ በተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ተፈጥሮ በሂሳብ አያያዝ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ተገቢ ማስረጃ መሰብሰብና ወደ ወጪነት መቀየር የማይችሉትን ደግሞ ለሂሳብ መዝገቡ እርምት እርምጃ በህጉ መሰረት በሚገባ መልኩ ለመስራት የስራ አመራሩ ወስኖ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹን ላይ ከፍተኛ ክትትል እያደረገ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 3. <u>**የተከፋይ ሂሳብ፣**</u>

### 3.1. <u>**በወቅቱ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ፣**</u>

3.1.1. <u>**ግኝት፣**</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ ‹‹ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀደ

ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት›› እና በንዑስ አንቀጽ ሐ ‹‹መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው›› መመሪያው ቢያመለክትም፣ ዩኒቨርሲቲዉ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ከአንድ አመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 104,068.99፣
2. ከ5 ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 15,499,533.65፣

በድምሩ ብር **15,603,602.64** በተከፋይ ሒሳብ ተይዞ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታዉቋል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 19 ተያይዟል)**

3.1.2. <u>ሥጋት፣</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

3.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ፣ ወደ ሀብት መቀየር ካለበት እንዲቀየር፣ ተገቢ ማስረጃ የሚቀርብ ከሆነ መከፈል ያለበት ሂሳብ እንዲከፈል ካልሆነም ለሂሳብ መዝገቡ የእርምት እርምጃ በህጉ መሰረት ሊወሰድ ይገባል፡፡

3.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከታየዉ ጠቅላላ የተከፋይ ሂሳብ ዉስጥ በአብዛኛዉ በ2013 የበጀት ዓመት መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ እጥረት ምክያት ያልተከፈሉ ሂሳቦች ሲሆኑ በ2014 ዓ.ም ክፍያዎች እየተከፈለ እንደሆነ ሊታወቅልን ይገባል፡፡

4. <u>በጀት፣</u>

4.1. <u>የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>

4.1.1. <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ

ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዉን የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ለዩኒቨርሲቲዉ ለ2013 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የመደበኛ በጀትና የካፒታል በጀት ወጪ በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ከመደበኛ በጀት ብር 60,591,987.21፣
- ከካፒታል በጀት ብር 295,388,847.49፣

በድምሩ ብር 355,980,834.70 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ ታዉቋል፡፡

**(ለዝርዝሩ አባሪ 20 ተያይዟል)**

4.1.2. ሥጋት፣

የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲዉን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

4.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

